# ከሞት ወደ ሕይወት

ለዚህ ገሀድ ዓለም ገዥ፣ ሠሪ፣ ናዛዥና ተቆጣጣሪ አካል አለው፡፡ይህ ታላቅ ፍጡር የተገኘው አንድ ኃይል አለ፣ በሚባለው ወይም በተፈጥሮ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ዓለምን እንደፈለገ የሚያሽከረክረው፣ እንደ መንፈሳዊ አስተምህሮ ከፍጥረታት በተለየ ሁኔታ ታላቅ የጸጋ ስጦታ የተሰጠው፣ እንደ ሳይንሱ ግኝት በተፈጥሮ ልዩ ኃይልና ጥበብ የተቸረው፣ አርቆ አሳቢው ሰው ብቻ ነው፡፡ ሰው ሲባል ደግሞ "positive and negative thinker" (ሠናይና እኩይ አሳቢ) መሆኑ አይካድም፡፡ እነዚህ ሁለት ተቃራኒ አስተሳሰቦች አብረው የሚኖሩና ወደ ተግባር የሚቀየሩ ናቸው፡፡

እስኪ አንድ ጥያቄ እናንሳ፡- ሰው ቀና (ጠቃሚ) የሆነውን ብቻ መርጦ ማሰብና መተግበር አይችልም? ለምሳሌ ሰው **በሕሊናው** አውጥቶ አውርዶ መልካም እያሰበ ሌሎች የስሜት ሕዋሳት መርጠው እንዲተገብሩ ማዘዝ ቢችል፣ ለምሳሌ በዓይን ብንጀምር፣ **ዓይን** በርካታ ነገሮችን ያያል፣ ካያቸው ነገሮች መጥፎዎችን እንዳላየ አይቶ በመተው ጠቃሚዎችን አስተውሎት ሰጥቶ እንዲመለከታቸው ቢያደርግ፣ መቸም ማየትና መመልከት ይለያያሉ፡፡

**ጆሮ፡-** አንደበት የሚናገረውን እንቶ ፈንቶውንም ሆነ ፍሬ ነገሩን ይሰማል፡፡መጥፎውን እንዳልሰማ አፍስሶ፣ " ደንቆሮ በጎ ኗሪ ሰሚ ነው ተቸጋሪ" ብሎ መልካም ተግባራት ላይ ብቻ አፅንዖት ሰጥቶ ማዳመጥ ቢጀምር፣ መስማትና ማዳመጥ ልዩነታቸው ይታወቃልና፡፡ **እጅ፡-** የሰው ደም ከማፍሰስና ሰው ከመግደል ተቆጥቦ ጠቃሚ ምክረ - ሀሳብ የያዙትን ጉዳዮችና ምርምሮች ቢጽፍ፣ እጅ ቀልጣፋ ስለሆነ ወንድሙ ሲወድቅ ሲያየው ቢያነሳው (ቢያቃናው፣) ሲቸገር ሲያየው ቢመጸውተው እና የመሳሰሉትን በጎ ተግባራት መርጦ ቢሠራ ጥሩ ውጤት ያስገኛል፡፡

**እግር፡-**ጉዞውን ወደ ስርቆትና ሕይወትን ወደሚያጠፋ ነገር ባይንቀሳቀስ፣ መንገዱ የዝንጀሮ መንገድ ባይሆን፣ የዝንጀሮ መንገድ ሂዶ ሂዶ ገደል ነውና፡፡ መንገዱ ቀና ሳይሆን ቀርቶ ሰው ችግር ሲደርስበት "እዚህ ስመጣ ምነው እግሬን በሰበረው" ይላልና፡፡ **አንደበት፡-** አስታራቂ ሀሳብ ያለውን ቃል ቢናገር፣ መርዝነት ያለው ቃል እየተፋና ነገር እየሠራ ሰውን ከሰው ባያጣላና ባያጋድል፣ እውነትን ቢደፍር፣ ሐሰትን ቢፀየፍ፣ ፈረስና ገብስን የሚያጣላ ሳይሆን አይጥና ድመትን የሚያስታርቅ ቃላትን ቢናገር ሰላም ይፈጠራል፡፡ምክንያቱም

ጦርነት ከፈታው ወሬ የፈታው ይባላልና፡፡ ለዚህ ሁሉ ነገር ሰው ለሕሊናው ታዛዥ ቢሆን ሁሉም የስሜት ህዋሳት ወደ ልማት እንጅ ወደ ጥፋት አይሠማሩም ነበር፡፡

ዓለምን ቆም ብለን በአስተውሎት ብንመለከት ወይም ጥናት ብናደርግ ሰው በየትኛው አስተሳሰብና ተግባር ላይ አመዝኖና ተሠማርቶ እየሠራ እንዳለ መለየት ይቻላል፡፡ ከአጠቃላዩ ሕዝብ መካከል ምሁሩ የኀብረተሰብ ክፍል ላይ አጽንዖት ሰጥተን ምልከታ ብናደርግ በአብዛኛው ጥፋት ላይ እንጅ ልማት ላይ ሲሠራ አናይም፡፡ ለምሳሌ የልማት መሣሪያ አምርቶ የሰው ጠላት የሆነውን ድህነት በመዋጋት ፈንታ ዓለምን ሊያጠፉ የሚችል የጦር መሣሪያ እየሰራ አፈ - ሙዝ እየተማዘዘና ተተኳሽ እየወነጨፈ ለእልቂት ይዳርጋል፡፡

ለዚህ መሣሪያ ማምረቻና ግዥ የሚውለው መዋዕለ - ንዋይ በአኃዝ ሊገለጽ የማይችልና ለልማት ቢውል የዓለምን ሕዝብ ከበሽታ፣ ከረሃብ፣ ከእርዛት፣ ከስደት፣ ከጉስቁልና፣ ከመከራና ወዘተ አስከፊ ተግዳሮቶች ይታደገው እንደነበር መገመት አያዳግትም፡፡ ይህንን ወደራሳችን ብናመጣው በሀገራችን ብሎም በክልላችን አሁን ላይ ያለው እውናዊ እንቅስቃሴ በትንሹም ቢሆን ለአብነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

የሰው ልጅ በርካታ ጉዳዮችን የሚመረምር መሆኑ የሚደገፍ ሆኖ ሳለ ተግባር ላይ የሚያውለው ራሱን የሚጎዳ ላይ መሆኑ ደግሞ ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም የተማረውን እውቀት ለጥቅም ካላዋለው " አህያ ሰባ ካልተበላ ምን ረባ" ነውና ተረቱ፡፡

ከዚህ ፅንሠ - ሃሳብ ጋር በተያያዘ ደራሲ ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ በረከተ መርገም በሚል ርእስ ባዘጋጀው ግጥም በከፍተኛ የፈጠራ ሥራ ስመ - ጥር የሆኑትን ሊቃውንት ካስገኙት የቴክኖሎጅ መሣሪያ ተነስቶ ሂሳዊ አስተያየት ሰጥቷል፡፡ከዚህ ውስጥ ቀንጨብ አድርገን የወሰድነውን ሀሳብ እንዲህ አቀርበናል፡፡

በአየር እርዳታ ጥረህ ተጣጥረህ ታግለህ ያገኘኸው፣

ልቅምቃሚ ወሬ እንቶ ፈንቶ ተረብ ለማዛመት ለሰው፣

ምኞትና ተስፋን፣ ድለላን ፍራቻን ለመስበክ ለመላው፣

ሬዲዮን ስትፈጥር ለውሸት ማወጃ ብለህ ከሠረህው፣

የዋሁ **ማርኮኒ** ነፍስህን አይማረው፡፡

በእኔነት አንቀልባ ታዝለው ለሚኖሩ ለህብታሞች ጥቅም፣

በየመንገዱ ላይ ደሃን እየገጩ ሕይወትን ለማውደም፣

ሕይወትን ለማጥፋት አስፓልት ማጨማለቅ እንደኔ ባለው ደም፣

ደግሞም ለማጭለጊያ አንዳንዲቷን ደማም፣

እንዲሆን ከሆነ የተግባርህ ግቡ ለጭከና አቋም፣

ደንቆሮ **ፋራዳይ ከመኪናህ ጋራ** ውቅያኖስ ስጠም፡፡

ስትሠሩ ከጥንቱ የአየር መንኮራኩር፣

ለመጫን ከሆነ አልባሌ ካልቸር፣

ደግሞም ማጓጓዣ ዝባዝንኬ ነገር፣

**ሮንግ ብራዘርስ** እንጦሮጦስ ግቡ **ከአውሮፕላኑ ጋር**፡፡

ሜራ ለመዶለት ግዳይ ለማዋሸክ እንዲመች ብለህ፣

ግፍን ለማማከር ጭቆናን ለማቀድ  ከሆነ ሀሳብህ፣

ችግርን ለማወጅ ተብትበህ ልትጥል በእነዚህ ተመርተህ፣

እንዲሆን ከሆነ **ቴሌፎን** መሥራትህ፣

ደደቡ **ግራሃም** ምድረ ፋይድ ያውርድህ፡፡

የእነዚህ ተመራማሪ የሥራ ውጤት ቀላል (ጎጅ) ሆኖ አይደለም፡፡ዋናው ምክንያት ሰዎች ማንኛውንም ሥራ ሲሠሩ ጥቅሙን ብቻ ሳይሆን ጉዳቱንም ማጤን እንዳለባቸው ለመጠቆም ሲሆን መነሻ ሀሳባችን ትልቅ አእምሮ ያለው ሰው ትልቅ ጥፋት መሥራት የለበትም፡፡ ምክንያቱም ሰው ሰውን ሲገድል ራሱን መግደሉ እንደሆነ ለአፍታም ሊዘነጋ አይገባም፡፡ እንዴት ቢባል ምላሹ ሰው ሰው ነውና፡፡ ከዚህ አንፃር ገጣሚው እነርሱንም ለጉዳት አልማችሁ ከሠራችሁት ትክክል አይደላችሁም ለማለት ነው፡፡ ጠቅለል ሲል

ሀሳባችንና ተግባራችን በሙሉ ቀና (ጠቃሚ) ይሁን ለማለት ነው፡፡ ሰው ቀና ነገር አስቦና እውነትን ተናግሮ መልካም ከሠራ በሁለት በኩል ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ አንድም በዚህ ዓለም ሲኖር በማኅበረሰቡ ተወዳጅ ስለሚሆን በሕይወተ-ሥጋው ደስተኛ ይሆናል፡፡ሌላው እንደ መንፈሳዊ አስተምህሮ በማያልፈው ዓለም ከሞት በኋላ ባለው ሕይወት እንደ አፈጣጠሩ ታላቅነት ታላቁን ቦታ ይይዛል፡፡ ስለዚህ ወጣቱ፣ አዛውንቱ፣ ሴት ወንዱ ለጥላቻና ለጦርነት ቦታ መስጠቱን ትተን ለሰላምና ለልማት እንነሳ! ሰላምን ለመፍጠር ሰው ከሰው ጋር መቃቃር ሳይሆን መድኃኒቱ መፈቃቀር ነው፡፡ በማለት የዛሬውን በዚህ አጠናቀቅን፡፡ ሰላም ለሁላችሁ!! ይበለን፡፡

ዝግጅት በፍሬው ምናለ